# የሰለባ/ምስክር እርዳታ ፕሮግራም
(Victim/Witness Assistance Program)

**የሰለባ/ምስክር እርዳታ ፕሮግራም ምንድነው?**

የአሰቃቂ ወንጀል ሰለባ ወይም ምስክር ከሆኑ ፍርድ ቤት መቅረብ ይኖርብዎት ይሆናል።

ይህ አስቸጋሪና ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ስለ ወንጀለኛ መቅጫ ፍርድ ቤትና ስለሚጠበቅብዎት ነገር ብዙ ጥያቄዎች ሊኖርዎት ይችላል።

የሰለባ/ምስክር እርዳታ ፕሮግራም ሊረዳዎት ይችላል። እናነጋግርዎትና የግል ጉዳዮንና የሚያስፈልጉዎትን ነገሮች አይተን እንረዳዎታለን።

አገልግሎታችን የሚጀምረው የፖሊስ ክስ ከቀረበ በኋላ ሲሆን የፍርድ ቤት ጉዳዩ እስከሚያልቅ ድረስ ይቀጥላል።

**እርዳታ ማግኘት የሚችለው ማነው?**

አገልግሎቶች በቅድሚያ የሚቀርቡት ለአሰቃቂ ወንጀል ሰለባዎችና ምስክሮች፣ ለምሳሌ በቤተሰብ አባል ላይ የሚከሰት በደል፣ የሕጻናት በደል፣ የመድፈር ጥቃት፣ የአዛውንት በደል፣ ነፍስ ግድያ እና የጥላቻ ወንጀልን የመሳሰሉ።

በተጨማሪ ለሚከተሉት እርዳታ እናቀርባለን፦

- የተለየ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ሰለባዎች
- ሕይወታቸው የጠፋ ሰዎች ቤተሰቦች
- የወንጀል ክስ ያስከተሉ ከባድ የመኪና አደጋዎች ሰለባዎች ቤተሰቦች

ከዕድሜ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ መረጃና አገልግሎት ለልጆች አለ።

**እርዳታ የማገኘው እንዴት ነው?**

ክስ ከቀረበ በኋላ ፖሊስ ወይም የዘውድ አቃቤ ሕግ፣ ሰለባዎችና ምስክሮችን ለእርዳታ ወደ ፕሮግራሙ ያስተላልፋሉ። የአሰቃቂ ወንጀል ሰለባ ከሆኑ፣ ፕሮግራሙ ጋር በግልዎ መደወል ወይም በርስዎ ስም አንድ የማህበረሰብ አባል እንዲደውልልዎት ማስደረግ ይችላሉ። እርዳታ ለመስጠትና ማንኛውም የደህንነት ጥያቄዎችዎን ለመመለስ ሠራተኞች በተቻለ መጠን በፍጥነት ይደውሉልዎታል።

**ክፍያው ስንት ነው?**

አንተሪዮ ውስጥ በሙሉ አገልግሎቶች ነጻ ናቸው።

**ምን ዓይነት እርዳታ ይገኛል?**

የሰለባ/ምስክር እርዳታ ፕሮግራም የሚከተሉትን ማድረግ ይችላል፦

- ስለወንጀለኛ መቅጫ ሥርዓት፣ ስለ ፍርድ ቤት ሂደቶችና በፍርድ ቤት ውስጥ ስለሚኖርዎት ሚና ለሚኖርዎት ጥያቄዎች መልስ መስጠት
- እያንዳንዱ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ ምን ሊጠብቅዎት እንደሚችል እንዲረዱ እርዳታ፣ እንዲሁም ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ሲዘጋጁ እርዳታ ማቅረብ
- በዋስ ስለመለቀቅ ሁኔታዎችና የተባባሪነት የፍርድ ቤት ውሳኔ የመሳሰሉ የፍርድ ቤት ሰነዶች ኮፒ ለእርስዎ ማቅረብ
- የዘውድ አቃቤ ሕጉን ወይም ፋይልዎን በመከታተል ላይ ያለውን ፖሊስ መኮንን በስምዎ መገናኘት
- በፍርድ ቤት ሂደቱ ላይ በቀጣይነት የሞራል ድጋፍ አቅርቦት ማድረግ
- ሌሎች የምክርና የደህንነት አገልግሎቶችን ማግኘት እንዲችሉ ወደተለያዩ የማህበረሰብ ግልጋሎት ሰጪ ድርጅቶች ሊያስተላልፍዎት ይችላል
- ለቤተሰብ ጥቃት ጉዳዮች የቋንቋ አስተርጓሚዎች ማዘጋጀት እና/ወይም ልዩ እንክብካቤ የሚያስፈልጓቸውን ማስተናገድ
- የሰለባ ተጽዕኖ መግለጫውን እንዲረዱና እንዲሞሉ እርዳታ ማቅረብ።

ፕሮግራሙ የሚከተሉትን ማድረግ አይችልም፦

- ማስረጃዎትን መረከብ ወይም ስለሱ መወያየት
- ክስን መሰረዝ
- የልጅ ጥበቃ እርዳታ ማቅረብ ወይም ማዘጋጀት
- ወደ ፍርድ ቤትና ከዛ መልስ መጓጓዣ ማቅረብ።

**ፕሮግራሙን የምገናኘው እንዴት ነው?**

የሰለባ/ምስክር እርዳታ ፕሮግራም በጠቅላይ አቃቤ ሕግ ሚኒስቴር በ54ቱም የዞን ፍርድ ቤቶች ውስጥ ቀርቦ ይገኛል።

በአካባቢዎ የሚገኘውን ቢሮ ለማግኘት ወደሚከተለው ይደውሉ

**የሰለባ ድጋፍ መስመር**

በነጻ 1-888-579-2888 ወይም

ታላቁ የቶሮንቶ አካባቢ 416-314-2447

ወይም የሚከተለውን ይጎብኙ

www.ontario.ca/victimservices